www.xtrapapers.com

M12/1/A1AMH/SP2/AMH/TZ0/XX

22120016

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Tuesday 15 May 2012 (morning)
Mardi 15 mai 2012 (matin)
Martes 15 de mayo de 2012 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.
- The maximum mark for this examination paper is *[25 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est *[25 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[25 puntos]*.


© International Baccalaureate Organization 2012

www.xtrapapers.com



*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳያ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ያፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ **ያልተመሰረተ** መልስ ከፍተኛ ነጥብ **አያስገኝም**::*

**ድራማ**

1. ጻሀፌ ተውኔቶች የተወሰኑ የድራማ ቴክኒኮች በመጠቀም የሰውን ልጆች ግጭት እንዴት እንዳሳዩ አስረዳ:: መልስህ ያጠናሃቸውን በተለያዩ ጻሀፌ ተውኔቶች የቀረቡ ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት የሚጠቅስ ይሁን::

2. ቋንቋ ተናጋሪውን ይገልፃል:: ቋንቋ ገፀባህርያትን ለማቅረብ ያለውን ጠቃሚነት ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ አስረዳ::

**ረጅም ልቦለድ**

3. የልቦለድ ርእስ በአብዛኛው ልዩ ጥቅም አለው:: የተለያዩ ደራስያንን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ የልቦለዶቹ ርእሶች ከስራዎቹ ጋር ያላቸውን ዝምድናና አጠቃላይ ጥቅማቸውን አብራራ::

4. የልቦለዶች ጭብጦች በአብዛኛው በለውጥ ላይ ያተኩራሉ:: እነዚህ የለውጥ ጉዳዮች እንዴትና ለምን እንደቀረቡ ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ምሳሌነት አስረዳ::

**ስነግጥም**

5. ገጣምያን አዲስና ያልተጠበቁ የህይወትን ገጽታዎች ለማስተላለፍ የሚጠበቁባቸውን ዘዴዎች በማወዳደር አስረዳ:: መልስህ ያጠናሃቸውን በተለያዩ ገጣምያን የቀረቡ ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በምሳሌነት የሚጠቅስ ይሁን::

6. ግጥሞች በአብዛኛው ተቃራኒ ስሜቶች ለምሳሌም ደስታና ሀዘን &ተስፋና ጥርጣሬን ያሳያሉ:: ያጠናሃቸውን በተለያዩ ገጣምያን የቀረቡ ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመውሰድ ደስታና ሀዘን &ተስፋና ጥርጣሬ እንዴት እንደቀረቡ አሳይ::

www.xtrapapers.com



**ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)**

7. ማንኛውም ጥሩ ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) አሳማኝ ሊሆን ይገባል:: ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ደራስያኑ በምን አይነት መንገድና በምን ያህል ደረጃ አሳማኝ እንደነበሩ አስረዳ::

8. የማንኛውም ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ጻሀፍያን የግል ልምዳቸውን መሰረት አድርገው በህብረተሰቡ ላይ አስተያየት ይሰጣሉ:: ያነበብካቸውን የተለያዩ ጻሀፍያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ሃሳቡን አስረዳ::

**አጭር ልቦለድ**

9. ባጠናሃቸው የተለያዩ ጻሀፍያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ሁኔታዎች የሚለወጡበት ወሳኝ ወቅቶች እንደምን እንደቀረቡ በንጽጽር አስረዳ:: ወሳኞቹ ወቅቶች ለአጭር ልቦለዶቹ የነበራቸውን አስተዋጽኦ አብራራ::

10. ያጠናሃቸውን የተለያዩ ጻሀፍያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ንኡስ ገፀባህርያት ለአጭር ልቦለዶቹ ያላቸውን አስተዋጽኦና አቀራረባቸውን አወዳድር::

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

11. ስነጽሁፍ ጠቀሜታው የጎላው ውበት ያለውና ስሜታችንን የሚነካ በመሆኑ ነው:: የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት ባጠናሀቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ምሳሌነት አስረዳ::

12. ስነጽሁፍ ነገሮች ሁልጊዜ እንዳሰብናቸው እንደማይሄዱ ያሳየናል:: ያጠናሀቸውን የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር የሃሳቡን ትክክለኛነት አሳይ::

13. ባጠናሀቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ ተፈጥሮን እንዴት እንዳቀረቡና በአጠቃላይም ተፈጥሮ ለስራዎቻቸው እጅግ ጠቃሚ መሆኑን እንዴት እንዳሳዩ አብራራ::

14. ደራስያን የልጅነት ህይወትንና ወጣትነትን በስራዎቻቸው እንዴትና ለምን አላማ እንዳቀረቡ አሳይ:: መልስህ ያጠናሃቸውን በተለያዩ ደራስያን የቀረቡ ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት የሚጠቅስ ይሁን::

---